ይህ ወር …-3

ባለፈው አንድ መቶ  አስር ዓመት ግዜ ውስጥም በሁለቱም አገሮች ውስጥና በመላው ዓለም የተከሰቱትን የፖለቲካና ማህበራዊ፣ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ለውጥና እድገቶችን እየተከተለ የሁለቱ አገሮች ግንኙነትም ተለዋውጧል;; የሩስያው የጥቅምት አብዮት ፤ የሁለተኛው ዓለም ጦርነት ፤ የኢትዮጵያ አብዮት ፤ የቀዝቃዛው ጦርነት ማክተም.. ወዘተ ለግንኙነታቸው መላላትም ሆነ መጥበቅ ምክንያት በመሆን ብዙ ጠመዝማዛ መንገዶችን አለፎ ዛሬ ላለበት ደረጃ በቅቷል;; ሁሌም ቋሚ ቀሪ የሆነው የሁለቱ አገር ህዝቦች ወንድማዊ ስሜት፣ በጎ ምኞትና መደጋገፍ ግን ዛሬም እንደ ጥንቱ የጸና ይሆናል;;

በግርድፉና በጥቅሉ የሁለቱን አገሮች የታሪክ ሂደትም ሲስተዋል ብዙ ተመሳሳይነት ጣምራነት /parallel/ይታይበታል;;

ባለፉት ዘመናት ሁለቱም አገሮች የአፄዎችን የ " ገብር ወይ አስገብር " ስርዓተ-ትውልድ አልፈው፣ የ "ጠቅልል ወይ ተጠቅለል" የኢምፓየሮችን የጫካ ህግ ዘመን ተሻግረው ከዛም የሶሻሊስት አብዮትና የወዛደር አምባገነንነትን ስርዓት ታመውና ድነው፣  በያዝነው አዲስ ምእተ ዓመት የግለሰብ መሰረታዊ የዲሞክራሲ መብቶችን ምሶሶው ያደረገና የህዝቦችን ነፃነትና ስልጣን ያረጋገጠ ስርዓት ለመመስረት በሂደት ላይ ይገኛሉ;; በሁለቱም አገሮች ሁለቱም ኢምፓየሮች ፈርሰው በህዝቦች ፈቃድና ስምምነት ላይ የተመሰረተ አንድነትና አዲስ አገር የመገንባት የአዲስ ሚሊኒየም ጎዳናም ጀምረዋል;;

በዓለም አቀፍ ደረጃም ሀያላን መንግስታት የሚፈልጡበት የሚቆርጡበት ዘመን ተወግዶ አዲሱ ዓለም አቀፍ ስርአት - multi-polar system - እየተገነባ ፤ አዲስ የአካባቢ ሀይላት / emerging regional powers / ተደማጭነት እየሰፋ ባለበት አዲስ ዘመን ሁለቱም አገሮች ለዘህ ስርአት ማደግ የበኩላቸውን አስተዋፅኦ በጋራ የሚያበረክቱበት ግዜ ይሆናል;;

አዲስ የአካባቢ ሃይላት / emerging regional powers /ከተነሳ ኢትዮጵያም እንደ ሩስያ ወይም እንደ ህንድ፣ ቻይና ብራዚል ... ወዘተ የአካባቢው ጠንካራ አዲስ ሀይል  ሆኖ ለመውጣት ሁሉም አይነት እድልና ችሎታ /potential/ ያላት ሲሆን ከዚህ ለመድረስ ግን እስካሁን የተገኙትን አዎንታዊ እርምጃዎችን ጠብቆ አሉታዊ መሰናክሎችን መቋቋምና ማለፍ ወሳኝ ቅድመ-ሁኔታ ይሆናል;;

ከሁሉ በፊት ለአገሪቱ እድገት ትልቁ ቅርስና ሃብት የሆነው የህዝቦችን ነፃነትና እኩልነትና መሰረቱ አድርጎ የተገነባውን አዲስ አንድነትና የአገሪቱን ልዕልና ማስጠበቅ የመጀመሪያው ቅድመ ሁኔታ ይሆናል;; ዛሬ ይህንን የሚፈታተኑ የትናንት ሀይሎችና የዛሬው ግዜ ተስፈንጣሪዎች እውን መሰናክሎች ሆነው ይገኛሉ;;

በአንድ በኩል ለዘመናት ከአያት ከቅድመ አያት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ድቅድቅ ጭለማ /Ignorance bigotory/ የትናንትናዋን ኢትዮጵያ ለመመለስ የሚሻ መንፈስ፣  በሌላ በኩል ደግሞ ኢትዮጵያና  ኢትዮጵያዊነት የሆነ ነገር ሁሉ ለማጥፋት የተነሳ ጥንፈኛና በቀለኛ አፍራሽ ሃይል በተናጥልና በጋራ ሆነው (እንደ AFD ማለት ነው) አገሪቷን አምሰው ካልበተኗት በስተቀር ኢትዮጵያም አዲስ የአካባቢ ሃይል ሆና የምትወጣበት ግዜ ሩቅ አይሆንም;;

የድንቁርና ጉዳይ ከተነሳ ዘንዳ በአንባቢ ፈቃድ አንድ ሁለት ልበል;;  በዘመናችን የአገሮች ጦርነት፣ የፖለቲካና የማህበራዊ ቀውስ ሁከትና ብጥብጥ ሁሉ ምክንያት ድንቁርና ነው;; በግል ህይወትም ድንቁርና የቅጥፈት፣ የብልግና የክፋት ሁሉ ምንጭ  ነው;; ድንቁርና በውስጣችን ያለውን መልአክ አስሮ በውስጣችን ያለውን ሰይጣን ፈትቶ የሚለቅ የጭለማ ሃይል ነው;;  የናዚን የኮንሰንትሬሽን ካምፕ የፈጠረ ድንቁርና ነው;; የሩዋንዳን ጭፍጨፋ ያመጣው ድንቁርና ነው;; የኬንያን የደም መፋሰስ አርግዞ የወለደው ድንቁርና ነው;; በመላው አፍሪካና በአካባቢያችን አንፃራዊ ሰላምና መረጋጋት ያላትና የእድገት ተምሳሌ የሆነችው ኬንያ ውስጥ ዛሬ ያየነውን ሩዋንዳን የሚያስታውስ

ክስተት ይመጣል ብሎ ማን ያሰበ አለ? ማን የገመተስ አለ? ማንም;; ምርጫና ፖለቲካ ሁልግዜ ሰበብ ነው;; የእርስ በርስ ግጭትና እልቂት እትብቱ የተቀበረው ሰዎች ልብ ውስጥ ባለው ጭለማ - ድንቁርና ውስጥ ነው;;

አገራችን ውስጥስ  ተመሳሳይ ሁኔታ ላለመከሰቱ ምን ዋስትና አለን? ማንስ በእርግጠኝነት መናገር ይችላል? ማንም;; ምክንያቱም ሩዋንዳም ውስጥ ሆነ ኬንያ ሰው ያጫረሰ ድንቁርና እኛም ውስጥ ተንሰራፍቶ አለ;; ድንቁርና ዩኒቨርሳል ባህርይ ያለው ነው;; የእኛም ድንቁርና እንደ ሩዋንዳውና ኬንያው ጎዳና አውጥቶ አላስተራረደም ወይም እድሉን አላገኘም እንጂ በየቤቱ በየጓዳውና በየሰዉ ልብ ውስጥ ተከናንቦና አሸልቦ እንደተቀመጠ ነው;; ራሱን አውጥቶ በገሃድ  የሚያሳየውና አደባባይ ወጥቶ 'አለሁ! አለሁ!' የሚለው ኢንተርኔት ላይ ፓልቶክና ፎረሞች ላይ ነው;; የጥላቻ ፖለቲካ ፣ ሃኬት፣ እብሪትና ከእኔ ወይም ከእኛ በላይ ገደል - የድንቁርና መለዮ፣ የደናቁርት ሱፍና ክራባት ናቸው;;

ቲቪ ስክሪን ላይ ትናንትና ሩዋንዳ ዛሬ ኬንያ ውስጥ ቆንጨራና ገጀራ ይዘው ወንድ ሴት፣ ህጻን ሽማግሌ ሳይሉ ሲጨፈጭፉና ቤተ-ክርስቲያን ሲያቃጥሉ የነበሩትን ሰዎች ልብ ብላችሁ ተመለከታችኋል? ኢንተርኔት ላይ ተመሳሳዩን የጥላቻና የብጥብጥ ቆንጨራና ገጀራ ከሚሰብቁት ወገኖቻችን በምንድነው የሚለዩት? በምንም;; ዜግነታቸው እንጂ የመንፈስ አባትና እናታቸው አንድ የዘር ግንድ ያለው ነው - ድንቁርና;;

የድንቁርና ሌላው ክፋቱ በትምህርት ልቀት ወይም በእድሜ ብዛት ታጠበው የሚጠሩት አለመሆኑ ነው;; ያ ቢሆን ኖሮ በአገራችን ከተማረው ክፍል ስንት ምሉዐ-ስብእና /integrity/ ያላቸውን ምሁራን ባገኘን ነበር;; "በለው" "ጣለው" "ገርስሰው" ከሚለው ይልቅ "አንድነት" "ሰላም" "ፍቅር" የሚሉት ድምፀ-ቃሎች በፖለቲካ ዲስኩሮች ውስጥ በገነኑ ነበር;;  ከስልጣን-ጥሙ ፖለቲከኞች  /power mongers/ ይልቅ አገረ-መንግስትነትን የሚያሰቀድሙ /statesman/ በበዙልንና ነበር;;

ከድንቁርና ለመታደግ የትምህርት ምጥቀትና የእድሜ ርቀት ብቻውን ዋጋ የለውም;; ብርሀነ-ህሊናን /enlightment/ ይሻል;; ትምህርት በዚህ ወይም በዛ የእውቀት መስክ አዋቂና ስልተ-እሳቦታችንን ያዳብር እንደሁ እንጂ ሙሉ የሰው-ነት ባህሪን ማጎናጸፍ የሚችል ዋሰትና ለሆን አይችልም;; አይደለምም;;  በዘመናዊ ትምህርት ሳይክቾለቾል ማሳው ላይ ውሎ የሚገባው የአገሬ ገበሬ ከተማረው ይልቅ ህሊናው የበራ ስብዕና አለው;; ብርሀነ-ህሊና የሚገኘው ደግሞ የሰው ልጆች የዘመናት የህይወት ልምድ ካፈራው የእውቀት ፍሬ /conventional wisdom/ በመቋደስ ነው;; በብርሀነ-ህሊና የሚቃኙበት ትምህርት ቤትም ህይወት ራሱ ነው;; ደግና ክፉውን /good and evil/ ለመለየት ድግሪ አያሻም;; ራስንና ሌላውን በጥልቀት መረዳት ነው;; ብርሀነ-ህሊና ማለት መንፈሳዊ ተፈጥሮን ማነጽ ፤ በውስጣችን ያለውን መልአክ መንከባከብ ማለት ነው;; ፖለቲካም እንደ ሌላው ሁሉ ከዚህ ጥበብ /conventional wisdom/ ላይ ካልተመሰረተና በዚህ ካልተመራ ውጤቱ የደግ ሳይሆን ምንግዜም የክፉ/evil/ ነው;;  የሩዋንዳና የኬንያ አይነት ምስቅልቅል፤ ደም መፋሰስና የአገር መበተንን ያመጣል;;

የብዙ ብሄርና ብሄረሰቦች የሆናችው አገራችን አንድ ቀን በጎረቤቶቻችን በኬንያ፣ ሩዋንዳና ሶማልያ ጎዳና እንደማትሄድ ሙሉ ዋሰትና ባይኖርም ትልቁ መተማመኛና ተስፋ የአገራችን  ህዝቦች አርቆ አስተዋይነትና ታጋሽነት ነው;;  በአንድ መንግስት ጥላ ስር ሆነውም ሆነ የየራሳቸውን ማህበራዊ ስርአት ይዘው ለሺህ ዓመታት ጎን ለጎን ሲኖሩ የቆዩት የአንድ ቤተዘመድ ሕዝቦች |ለዘመናት ያፈሩት አብሮ የመኖር ባህልና ጥበብ ዋናው የተስፋ መከታና ጋሻ ነው;; ይህም  "በተማሩ" ሰዎች የድንቁርና ሃይል ተገፍቶ፤ የህሊና ሚዛኑ ተፋልሶ ህዝቡን  በነሱ መንገድ ካልመሩትና ጎዳና ካላወጡት ይሆናል;;

ይቀጥላል